የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐ ረ ር ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| 10ኛ ዓመት ቁጥር 7<br>10th year No 7 | ሐረር መጋቢት 2 ቀን 1998<br>Harar march 11/2006 |
|---|---|

| ያንዱ ዋጋ ብር 4:00<br>Unit Ptice Br.4:00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272<br>P.O.Box 272 |
|---|---|---|

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር 11/1998

የሐረሪ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ ........................ ገጽ288

## ደንብ ቁጥር 11/1998

## የሐረሪ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ

በአሁኑ ወቅት ያለዉ የመሬት አጠቃቀም የመጪዉን ትዉልድ አኗኗር የሚጎዳ ሆኖ በመገኘቱና መሬትንና የተፈጥሮ ሃብትን ሥርዓት ባለዉ መንገድ ለመንከባከብ የህግ መሰረት መጣል በማስፈለጉ ፤

ግብርና-መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂንና የገጠር ልማት ፖሊሲዎችን ይበልጥ ተግባራዊ ለማድረግና የመሬትን ለምነትና የተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ ለመጠበቅና ለመጠቀም እንዲቻል ፤

በህዝብ ብዛት ምክንያት የእርሻ መሬት ይዞታዎች በየጊዜዉ እያነሱና እየተጣበቡ በመምጣታቸዉ ዘመናዊ የግብርና ዘዴዎችን ለመተግበር አመቺ ባለመሆኑ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የተሻለ የይዞታ ሥርዓት ማስፈን በማስፈለጉ ፤

የተፈጥሮ ሃብት መመናመን አደጋን ከመቀነስ አኳያ አርሶ አደሩ በይዞታዉ የመጠቀም መብቱ እንዲጎለብትና አስፈላጊዉን እንክብካቤ እንዲደረግ ምቹ የሕግ-ሁኔታዎች መፍጠሩ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

መሬትና የመሬት ሃብትን በዕቅድ ለመጠቀም፣ መሬትን በተመለከተ ለሚነሱ ግጭቶች ፤ አለመግባባቶችና የአጠቃቀም ችግሮች የሕግ መሰረት ያደረገ የመፍትሄ እርምጃ መዉሰድና የአስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ፤

የሴቶችና የመሬት ይዞታ ባለቤትነትና የመጠቀም መብት ያለምንም ተፅዕኖ ለማረጋገጥ እንዲቻል ፤

የሐረሪ ህዝብ ክልል ም/ቤት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀጽ 17 እና በተሻሻለው የሐረሪ ህ/ብ/ክ/ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ51ንኡስ አንቀጽ 2(ተ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል::

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ «የሐረሪ ሕ/ብ/ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 11 1998 ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ :-

1. «ክልል» ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልል ማለት ነዉ::
2. «መንግስት» ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነው::
3. "ቢሮ" ማለት የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ነዉ::
4. "መስተዳድር ምክር ቤት " ማለት የክልሉ ከፍተኛ የህግ አስፈጻሚ ስልጣን የተሰጠዉ አካል ነዉ::
5. " የገጠር መሬት" ማለት ከማዘጋጃ ቤት ክልል ዉጪ ወይም የሐረሪ ክልላዊ መንግሥት አግባብነት ባለዉ ህግ ከተማ ብሎ ከሚሰይመዉ አካባቢ ዉጪ ያለ መሬት ነዉ::
6. " የገጠር መሬት አስተዳደር " ማለት በገጠር መሬት ይዞታ ላይ ዋስትና የሚሰጥበት ፣ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሚተገበርበት ፣ በገጠር መሬት ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱትን ግጭቶች የሚፈቱበትና የማንኛዉም የገጠር መሬት ተጠቃሚ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ መሰረት የሚተገበርበት ሂደት ሥርዓትና ደንብ ማለት ነዉ::
7. " የገጠር መሬት አጠቃቀም " ማለት የገጠር መሬትን በእንክብካቤ ይዞ ዘላቂነት ባለዉ መንገድ ለተሻለ ጠቀሜታ እንዲዉል የሚደረግበት ሥርዓት ነዉ::
8. " የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ" ማለት አካባቢያዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የገጠር መሬት ሊሰጥ ከሚችለዉ አማራጭ፣ ጥቅሞች መካከል የመሬት መጎሳቆልንና የአካባቢን ብክለት ሳያስከትሉ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙት አማራጮች የሚወሰኑበትና ተግባራዊ የሚደረጉበት የአሰራር ዘዴ ነዉ::
9. " አርሶ አደር " ማለት የገጠር መሬት የይዞታ መብት ያለውና ከመሬቱም በሚያገኘዉ ገቢ እራሱን ወይም ቤተሰቡን የሚያስተዳድር አንድ አባወራ ወይም ዕማወራ ማለት ነዉ::
10. «የይዞታ መብት» ማለት ማንኛዉም አርሶ አደር የገጠርን መሬት ለግብርናና ለተፈጥሮ ሃብት ልማት ተግባር ላይ ለማዋል፣ ለማከራየትና ለቤተሰቡ አባልና ለሌሎች በህግ መብት ለተሰጣቸዉ ወራሾች ለማዉረስ የሚኖረዉ መብት ሲሆን ፣ በመሬቱ ላይ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ ንብረት ማፍራትን ይህንንም መሸጥ ፣ መለወጥና ማዉረስንም ይጨምራል::
11. "የቤተሰብ አባል" ማለት የይዞታ ባለመብቱን መተዳደሪያ ገቢ በመጋራት በቋሚነት አብሮ የሚኖር ማንኛዉም ሰዉ ነዉ::
12. "ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ ነዉ::
13. "የመሬት ተጠቃሚ" ማለት መሬትን ለመጠቀም መብት ያለዉ በገጠር መሬትን የሚጠቀም ግለሰብ ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ማለት ነዉ::
14. " የግል ይዞታ " ማለት በአርሶ አደሮች ወይም በሌሎች የመጠቀም መብት የተሰጣቸዉ አካላት እጅ ሆኖ ሕጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ወጥቶለት በግል ይዞታ ስር ያለ መሬት ነዉ::
15. " የወል ይዞታ " ማለት ከመንግስት ወይም ከግል ይዞታነት ዉጪ የሚገኝ እና የአካባቢ ነዋሪዎች በጋራ ይዞታነት የሚጠቀሙበት ሲሆን ፣ ለግጦሽ ፣ ለደንና ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች እየዋለ ያለ መሬት ነዉ::
16. " የመንግስት ይዞታ " ማለት በመንግስት ተከልሎ የተያዘና የሚያዝ መሬት ሲሆን ፣ የማዕድን መሬቶችን ፣ የዱር እንስሳዎችን መኖሪያ ጥብቅ ቦታዎችንና ወንዞች የያዙት መሬትን ያጠቃልላል::
17. " ዝቅተኛ የይዞታ መጠን " ማለት ምርታማነቱ የአንድን አርሶ አደር ሕይወት ማኖር የሚችል የመሬት ይዞታ /ለአመታዊ ሰብል ፣ ለቋሚ ሰብል ፣ ለግጦሽ ፣ ለመኖሪያ ቤትና ጓሮን ጨምሮ/ መጠን ማለት ነዉ::
18. " ተፋሰስ " ማለት የአንድ ማፍሰሻ ክልል ፣ የተቀራረበና የሚወራረስ ፣ የጋራ የአየር ንብረት ያለዉ ፣ ጎርፍ ፣ ጅረቶችና ወንዞች ተሰባስበዉ በአንድ በር የሚወጡበት ቅርፅና ስፋት ያለዉ መሬት ማለት ነዉ::
19. "የምስክር ወረቀት " ማለት በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን ለማረጋገጥ አግባብ ባለዉ አካል የሚሰጥ ሰነድ ነዉ::
20. " የተፈጥሮ ሃብት " ማለት መሬትና በመሬት ላይ የሚገኙ ህይወት ያላቸዉና ሕይወት የሌላቸዉ የተፈጥሮ ስጦታዎች ማለት ነዉ::
21. " አግባብ ያለዉ አካል " ማለት በአዋጅ ቁጥር 47/97 አንቀጽ4 ንዑስ ቁጥር 3 መሰረት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት መስፈኑን ለመከታተል የተቋቋመ የገጠርና የግብርና ቢሮ ወይም አካል ማለት ነዉ::
22. "የመሰኖ መሬት" ማለት በአሁኑ ጊዜ በመስኖ እየለማ ያለዉና ለወደፊቱም በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት ነዉ::
23. " የተከለሉ ስፍራዎች " ማለት በልዩ ፊዚካላዊና ስነ-ሕይወታዊ ገጽታ ምክንያት አስፈላጊ በመሆኑ ተከለሉ አካባቢን ለመጠበቅና ለማልማት እንክብካቤ የሚደረግለትና ለዘለቄታዊ ጥቅም የሚጠበቅ የመሬት አካል ማለት ነዉ::

24. «አዋጅ» ማለት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን ለመወሰን የወጣ የፌድራል ነጋሪ ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 456/97 ማለት ነው ::

## 3. መሰረተ ሃሳብ

1. መሬት የመንግስትና የህዝብ የጋራ ሃብት ሲሆን፣ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መንገድ መለወጥ አይቻልም::
2. ሴቶች ከወንዶች እኩል በሁሉም የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስራዎች መብት ይኖራቸዋል::
3. የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፅንሰ ሃሳብ ሁሉን አቀፍ ባህሪ ስላለው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግኑኙነት በሚኖራቸው አካላት በቅንጅት የሚተገበር ይሆናል::
4. የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን በአግባቡ ለመምራት ህብረተሰቡ መንቀሳቀስ፣ መሳተፍና የውጤቱ ተካፋይ መሆን አለበት::

## 4. የጾታ አገላለጽ

በዚህ ደንብ ዉስጥ ለወንድ ጾታ የተደነገገዉ ለሴት ጾታም ተፈጻሚነት አለዉ ::

## 5. የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በሐረሪ ብሔራዊ ክልል ዉስጥ በሚገኝ በማንኛዉም ዓይነት የገጠር መሬት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ::

# ክፍል ሁለት

## መሬትን በይዞታ ስለማግኘት ፣ ስለመጠቀምና የይዞታ መብትን ስለማስተላለፍ

## 6. የገጠር መሬት ስለማግኘትና የመጠቀም መብት

1. ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ እድሜዉ ከ18 ዓመትና ከዛ በላይ የሆነ በግብርና የሚተዳደር እና ለወደፊትም በዚሁ መተዳደር የሚፈልግ የገጠር መሬት በነጻ የማግኘት መብት አለዉ::
2. አርሶ አደሩ ለጋራ ጉዳዮች ጠቀሜታ ማለትም ለግጦሽ ፣ ለማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች እና ለዕምነት የሚሆን መሬት የማግኘት መብታቸዉ እንደተጠበቀ ይቆያል::
3. ለአርሶ አደሩ በቅድሚያ ትኩረት በመስጠት ባለሃብቶች ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚያቀርቡት የልማት ዓላማዎች እና በክልሉ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት በገጠር መሬት የመጠቀም መብት አላቸዉ ::
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ወላጅ አልባ ልጆች ፣ አረጋዊያንና አቅመ ደካሞች እንዲሁም ሌሎች በተመሳሳይ ሁኔታ ዉስጥ ያሉ ግለሰቦች እንደማንኛዉም ዜጋ የመሬት ይዞታ ባለቤትነትና የመጠቀም መብት አላቸዉ::
5. ማንኛዉም የመሬት ተጠቃሚ /ተጠቃሚዎች/ በክልሉ አግባብ ላለዉ አካል በማመልከት የመጠቀም መብቱን ሊተዉ ይችላል::
6. ማንኛዉም መሬት ተጠቃሚ የመጠቀም መብቱ የሚያበቃዉ መሬቱ ለበለጠ የሕዝብ ጥቅም ሲፈለግ ብቻ ነዉ:: ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል::
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት ባለይዞታነት ሲቀየር የይዞታ መብቱን ያጣዉ ግለሰብ በቋሚነት የተሰሩ ንብረቶችን ፣ የተተከሉ ቋሚ የዛፍ ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ተክሎችን የማንሳት ወይም ካሳ የመጠየቅ ፣ በማሳዉ ላይ የተተከለዉ ተክል ደርሶ ምርቱን እስኪያነሳ የመቆየት ወይም ካሳ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ይሆናል:: ዝርዝር አፈፃጸሙ በሚወጣው መምሪያ ይወሰናል::
8. ማንኛዉም በመሬት የመጠቀም መብት ያለዉ የአርሶ አደር ቤተሰብ አባል ከቤተሰቡ በስጦታ ወይም በዉርስ የገጠር መሬት በይዞታ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነዉ:: የመሬት ይዞታ በስጦታ በሚተላለፍበት ጊዜ የቤተሰብ ስምምነት መኖር ይኖርበታል ::
9. ባልና ሚስት ከመጋባታቸዉ በፊት በግላቸዉ የነበራቸዉ የመሬት ይዞታ ከተጋቡ በኋላ እንደነበረ ሆኖ በጋራ በሚሰጣቸዉ የምስክር ወረቀት ዉስጥ የግል ይዞታቸዉን እንዲያስመዘግቡ ይደረጋል:: ትዳር ሲመሰረት በአንጻሩ የምስክር ወረቀት እድሳት ይካሄዳል:: ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል::
10. የባል ወይም የሚስት ወይም የሁለቱም አካባቢዉን ለቆ መሄድ ወይንም በሞት መለየት የቤተሰብ የመሬት ይዞታ የመጠቀም መብትን አያሳጣም::
11. ይህን ደንብ ለማስፈጸም ወደፊት አግባብ ባለዉ አካል የሚወሰነዉ የአንድ እርሻ ማሳ ዝቅተኛ መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ ባልና ሚስት በሚፋቱበት ጊዜ በስማቸዉ የተመዘገበዉን መሬት ከሁለት አንዳቸዉ የሚያሳድጉትን የልጆች ቁጥር ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት የመካፈል እኩል መብታቸዉ የተጠበቀ ነዉ::
12. በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ማንኛዉም የመሬት ተጠቃሚ የመጠቀም መብቱንና ይዞታዉን ያለማጣት ዋስትና አለዉ::
13. መንግስት በመሬት ባለቤትነቱ የወል የገጠር መሬት ይዞታዎችን እንደአስፈላጊነቱ ወደ ግል ይዞታነት እንዲቀየሩ ለማድረግ ይችላል::

## 7. ያገጠር መሬት ይዞታ መብትን ስለ ማስተላለፍ

1. ማንኛዉም በመሬት የመጠቀም መብት የተሰጠዉ ሕጋዊ አካል በመሬቱ ላይ በጉልበቱና በገንዘቡ ያፈራዉን ሃብት ለሌላ

ህጋዊ አካል የመሸጥ ፣ የማከራየት ፣ የማዉረስና በዋስትና የማስያዝ መብት አለዉ።

2. ማንኛዉም አርሶ አደር በይዞታዉ ስር ያለዉን መሬት የቤተሰብ ስምምነት መኖሩ ሲረጋገጥ የተወሰነውን መሬት የማከራየት መብት አለዉ።ዝርዝር አፈፃጸሙ በመመሪያ ይወሰናል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ መሬት የመከራየት መብት የሚኖራቸዉ በግብርና መተዳደር የሚፈልጉ አርሶ አደሮች ወይም የመሬት ተጠቃሚዎች ናቸዉ።

4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰዉ ንብረትን የመሸጥም ሆነ ለሌላ ሰዉ የማስተላለፍ መብት ንብረቱ ያረፈበትን መሬት አይጨምርም።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት አርሶ አደሮች መሬት በማከራየት መብታቸዉ ዉስጥ የኪራይ ዉልና ዓይነት ፣ የኪራይ ዘመን ፣ እና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸዉ ጉዳዮች አፈጻጸምን በተመለከተ ወደፊት በሚወጣዉ ዝርዝር መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

6. ወራሽ ያልተገኘለት መሬት ለመሬት አጦች ወይም መሬት ላነሳቸዉ አርሶ አደሮች ይከፋፈላል።

7. የመሬት ኪራይ ተቀባይነት የሚኖረዉ በክልሉ የገጠር መሬትን ጉዳይ በሚያስተዳድረዉ አግባብ ያለዉ አካል ሲመዘገብ ነዉ።

8. የገጠር መሬት በዉርስ በሚተላለፍበት ወቅት የሚተላለፈዉ የመሬት ይዞታ መጠን ከአነስተኛዉ የይዞታ መጠን በታች መሆን የለበትም።

9. ከዚህ ደንብ በፊት ያሉ የገጠር መሬት ኪራይ ባህላዊ ፣ ሐይማኖታዊ ህጋዊና ሌሎች ተመሳሳይ ዉሎች ከዚህ ደንብ ጋር እንዲጣጣሙና ተቀባይነት እንዲኖራቸዉ የሚደረግ ሲሆን በቀጣይ ደንቡን የሚቃረኑ ማናቸውም የፅሁፍ ዉሎችና ስምምነቶች ተፈጻሚነት አይኖራቸዉም።

10. በዚህ ደንብ አንቀጽ 7 መሰረት የግል ይዞታ በሚከራይበት ጊዜ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በአከራይ እጅ ይቆያል።

## 8. የገጠር መሬት ይዞታ ዋስትና ስለመስጠት

1. ማንኛዉም የይዞታ መብት የተሰጠዉ አርሶ አደር በመሬቱ የመጠቀም መብቱን የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግባብ ካለዉ አካል ይሰጠዋል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል።

2. ባልና ሚስት በጋራ ይዞታቸዉ ላይ በጥምር የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኛሉ።

3. ከአንድ በላይ ሚስት ያለዉ ባል ከአንዷ ሚስት ጋር ብቻ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚያገኝ ሲሆን የቀሩት በየስማቸዉ የባለ ይዞታነት የምስክር ወረቀት ያገኛሉ።

4. ከአርሶ አደሮች ዉጪ በሌሎች የመሬት ተጠቃሚዎች የተያዙ መሬቶችም የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ከአጠቃቀም ዕቅድ ጋር ይሰጣቸዋል።

5. የይዞታ መብት ለዉጥ በሚደረግበት ጊዜ በአንጻሩም የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እድሳትም ይደረጋል።

6. ማንኛዉም የይዞታ መብቱን የተወ አርሶ አደር ተሰጥቶት የነበረዉን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለሚመለከተዉ አግባብ ያለዉ አካል የመመለስ ግዴታ አለበት።

7. ለሚመለከተዉ አካል የተመለሰዉ መሬት የመሬት ይዞታ ለሌላቸዉ ወይም ላነሳቸዉ አርሶ አደሮች ይከፋፈላል።

## 9. በገጠር መሬት አጠቃቀምና ስለተጣሉ ገደቦች

1. አንድ ማሳ ከሁለት ወይንም ከዛ በላይ መከፈል ሲኖርበት እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 መሰረት ወደፊት በሚወጣዉ መመሪያ ከሚወሰነዉ የአንድ ማሳ ስፋት በታች ሆኖ ሲገኝ ባለድርሻዎች በጋራ እንዲጠቀሙ ይገደዳሉ።

2. መሬትን በአግባቡ ተንከባክቦ ካለመጠቀም የተነሳ በመሬት ላይ ጉዳት ሲደርስ እና በቅጣት ብቻ ሊታለፍ የማይችል ሆኖ ሲገኝ ተጠቃሚው የመጠቀም መብቱን እንዲያጣ ይደረጋል።

3. ማንኛዉም የመሬት ተጠቃሚ ያለበቂ ምክንያት አግባብ ባለዉ አካል ከሚሰጠዉ የጊዜ ገደብ በላይ መሬትን ጦም ካሳደረ የመጠቀም መብቱን ያጣል። የጊዜ ገደብ ዝርዝር አፈፃፀም በመመሪያ ይወሰናል።

4. ማንኛዉም ሰዉ ወይንም ድርጅት ያለ ይዞታ ዋስትና ማረጋገጫ መሬት ሲጠቀም ከተገኘ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የያዘዉን መሬት እንዲለቅ ይገደዳል። ለፈጸመዉም ድርጊት በሕግ ይጠየቃል።

5. መሬትን የሚከራይ ማንኛዉም ግለሰብም ሆነ ድርጅት በተከራየዉ መሬት ላይ አግባብ ያለዉ የመሬት አያያዝ ስራዎችን በኪራይ ዘመኑ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት።

## 10. የገጠር መሬት ይዞታን የስፋት መጠን ስለመወሰን

አንድን አርሶ አደር ከነ ቤተሰቡ ለማኖር የሚያስችል እና ትርጉም ያለዉ ምርት ወደማይሰጥበት ደረጃ እንዳይበጣጠስ ለመከላከል ዝቅተኛዉ የአንድ ማሳ የመሬት መጠን አግባብ ባለዉ አካል ይወሰናል።

## 11. የገጠር መሬት ይዞታን ኩታ ገጠም ስለማድረግ

አርሶ አደሮች በመሃከላቸዉ በሚኖረዉ ፍላጎትና ፈቃደኝነት ላይ በተመሰረተ ስምምነት የይዞታ

ማሳቸዉን ኩታገጠም እንዲያደርጉና እንዲያዋህዱ ይበረታታሉ፡፡

## 12· የገጠር መሬትን ስለ መለካት፣ ስለመመዝገብና ስለ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር፣

1· በግል ፣ በወል እና በመንግሥት ይዞታዎች ያሉ የገጠር መሬቶች ስፋታቸዉን በመለካት እና የመሬት አጠቃቀማቸዉና የለምነት ደረጃቸዉ በክልልና በየደረጃዉ በሚቋቋሙ የመረጃ ማዕከላት እንዲመዘገቡ ይደረጋል፡፡

2· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት የገጠር መሬት ይዞታዎች አግባብ ባለዉ አካል ተለክተዉ የይዞታ ድንበራቸዉን የሚያሳይ ካርታ ይዘጋጅላቸዋል፡፡

3· ማንኛዉም የገጠር መሬት ባለይዞታ አግባብ ባለዉ አካል የሚዘጋጅና የመሬቱን ይዞታ ስፋት ፣ አጠቃቀምና ሽፋን ፣ የለምነት ደረጃና አዋሳኞቹን እንዲሁም ኃላፊነትና ግዴታን የያዘ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲኖራቸዉ ይደረጋል፡፡

4· የገጠር መሬት በማን ይዞታ ስር እንደሚገኝ ከማን መሬት ጋር እንደሚዋሰን ደረጃዉ ምን ዓይነት እንደሆነ ለምን አገልግሎት እንደሚዉልና ባለ ይዞታዉ ምን መብትና ግዴታዎች እንዳሉበት የሚገልፅ መረጃ ተመዝግቦ አግባብ ባለዉ አካል እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

## 13. በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

1· የአርሶ አደሮች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የጊዜ ገደብ የለዉም፡፡

2· የሌሎች ባለይዞታዎች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ጸንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ አግባብ ያለዉ አካል በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 14. የገጠር መሬት ተጠቃሚዎች ግዴታዎች

1· የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን በአግባቡ የመጠበቅና የመንከባከብ ግዴታ አለበት፡፡ በመሬቱ ላይ ጉዳት ከደረሰ በመሬቱ የመጠቀም መብቱን ሊያጣ ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ የሚመለከተዉ አግባብ ያለዉ አካል በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

2· የመሬት ባለይዞታዉ አግባብ ባለዉ አካል መሬቱ እንዲለካ ወይም የቅየሳ ስራ እንዲካሄድ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

3· ማህበራዊ ተቋማት የግል ባለሃብቶችና ሌሎች መሬት ለማግኘት የልማት ዓላማና ዕቅዳቸዉን የሚያሳይ ተቀባይነት ያለዉ የፕሮጀክት ዶክመንት የማቅረብ ግዴታ አለባቸዉ፡፡

4· ማንኛዉም በመሬት የመጠቀም መብት ያለዉ ሰዉ ከኩታ ገጠም ጎረቤቱ ጋር ተባብሮ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

5· ማንኛዉም የመሬት ተጠቃሚ በዉሃ ማጠራቀሚያ ስፍራዎች ፣ እዚያ ላይ የተሰሩ የዉሃ ስትራክቸሮችና ተፋሰሶች ላይ

መልሶ የማልማትና የመጠበቅ ስራዎችን የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡

6· ማንኛዉም የመሬት ተጠቃሚ የአፈር መከላትን ከሚያባብሱ እንደ ደን መመንጠር ፣ ሸቅብና ቁልቁል ማረስ ፣ በዘፈቀደ የሚቀደዱ የዉሃ ማስወገጃ ባህላዊ ቦዮችን ያለማከናወን ግዴ ታ አለበት፡፡

7· ማንኛዉም የመሬት ተጠቃሚ እንደ ባህር ዛፍና ቁልቋል ያሉ የእፅዋት ዘሮችን እንዲሁም አደገኛና በቀላሉ ሊሰራጩ የሚችሉ የአረም ዘሮችን በእርሻ ማሳና ከዉሃ ምንጮች አካባቢ ያለመትከል ግዴታ አለበት፡፡

8· ማንኛዉም በመሬት የመጠቀም መብት ያለዉ ይዞታዉን በሚወጣዉ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሰረት ለማከናወን ይገደዳል፡፡

9· ማንኛዉም የመሬት ተጠቃሚ አርሶ አደር እና በግብርና ሥራ የተሰማራ ተሰርተዉ ያሉትንና የሚሰሩ የአፈርና ዉሃ መጠበቂያ አዉታሮችን የመጠበቅ የማቆየትና የመጠገን ግዴታ አለበት፡፡

10· ማንኛዉም በመሬት የመጠቀም መብት የተሰጠዉ አካል በመሬት ላይ በደረሰዉ የተፈጥሮ ጉዳትና በመሬቱ ተዳፋትነት ምክንያት ተበልተዉ ወደ ቦርቦርነትና ገደላ ገደል ከተለወጡ መሬቶች ፣ ከምንጮችና ከወንዞች እንደ አፈሩ ክለት አሳሳቢነት አግባብ ባለዉ አካል በመመሪያ ከሚወሰነዉ እርቀት አልፎ ያለመድረስና ከነዚህም ጋር የሚዋሰኑትን ቦታዎች የመጠበቅና መልሶ የማልማት ግዴታ አለበት፡፡

11· ማንኛዉም የገጠር መሬት ባለይዞታ በመሬቱ የመጠቀም መብቱን በፍቃዱ ሲተዉ አግባብ ላለዉ አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

12· በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያለዉ ማንኛዉም ሰዉ ወይም አካል የመሬት ተዳፋትነቱ ከ31- 60 % የሆነ የገጠር መሬት ለአመታዊ ሰብል ለማዋል ከፈለገ ጠረጴዛማ እርከን የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

13· ማንኛዉም የመሬት ተጠቃሚ ተዳፋትነቱ ከ60 % በላይ የሆነ የገጠር መሬት ለእርሻ እንዳያዉል ይገደዳል፡፡ ይሁንና በዚህ ደረጃ የሚገኝ መሬት ለዛፍ ፣ ለቋሚ ተክሎችና ለእንስሳት መኖ ልማት እንዲዉል ይደረጋል፡፡

# ክፍል ሶስት
# መሬትን ማጥናትና በዕቅድ ስለመጠቀም ፣ በዉል ስለተያዙ መሬቶችና በመሬት ላይ ስለሚነሱ ግጭቶች

## 15. መሬትን በዕቅድ ስለመጠቀም

1. የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ አዘገጃጀት አቅምን ያገናዘበና ደረጃ በደረጃ የሚፈጸም ሆኖ፣ አፈር ዓይነትን ፣ የመሬት አቀማመጥን ፣ የተዳፋትነትን ፡ የአየር ጸባይን ፣ የዕፅዋት ሽፋንን እና ሶሾዮ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ባካተተ መልኩና ተፋሰስን መሰረት ያደረገ የመሬት አጠቃቀም መሪ ዕቅድ በክልሉ መንግሥት ወጥቶ ተግባራዊ ይሆናል።

2. ወቅታዊ የመሬት አጠቃቀም ለዉጥ የሚካሄደዉ በጥናት የተደገፈ መረጃ ላይ ዕቅድ ሲወጣ እና በዚህ ዕቅድ ላይ ተመስርቶ ጥቅም ላይ እንዲዉል ሲደረግ ብቻ ነዉ።

## 16. በወል ስለተያዙ የገጠር መሬቶች

1. የወል ይዞታ ተጠቃሚዎች በወል መሬቶች ላይ የሚገኙትን ዕፅዋት ፣ የዱር እንስሳትና ሌሎች የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ሃብቶችን እና ታሪካዊ ቅርሶችን የመንከባከብ ኃላፊነት አለባቸዉ።

2. በወል ይዞታነት የሚታወቁ ጉብታዎች ፣ የተራቆቱና ምርታማ ያልሆኑ መሬቶች ፣ በቀላሉ ሊጎዱ የሚችሉ ተራራማ አካባቢዎችን በአግባቡ ለመጠቀም የህብረተሰብ ተሳትፎን መሰረት ያደረገ የአጠቃቀም ዕቅድ እንዲወጣላቸዉ ይደረጋል። እንዲሁም ወደ ግል ይዞታነት በመቀየር በተሻሻለ አሰራር ለደንና ለሌሎች ቋሚ ተክሎች የማዋል ኃላፊነት አለባቸዉ።

3. የወል ይዞታ ተጠቃሚዎች በህብረተሰቡ የሚወጡና ይህን ደንብ የማይቃረኑ የአካባቢ ሕጎችና ልማዳዊ አሰራሮችን በወል መሬቶች አጠቃቀምና አያያዝ ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖራቸዉ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸዉ።

## 17. በባለሃብት ስለሚያዙ መሬቶች

1. ባለሃብቶች በመሬት ለመጠቀም የሚያቀርቡት የልማት ዕቅድ በክልሉ የመሬት አጠቃቀም መሪ ዕቅድ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት።

2. ማንኛዉም ባለሃብት በዉሉ መሰረት በይዞታነት ከተሰጠዉ መሬት በላይ ያለመጠቀም እና ከተፈቀደለት የልማት ዕቅድ ዉጪ ያለመተግበር ግዴታ አለበት።

3. በመሬት አጠቃቀም መብት የሚሰጣቸዉ ባለሃብቶች በዚህ ደንብ ስለ መሬት አያያዝና እንክብካቤ ለተደነገጉ ድንጋጌዎች የመገዛትና በቀጣይ የሚወጡ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያዎችን የመፈጸም ግዴታ አለባቸዉ።

4. ማንኛዉም የመሬት ተጠቃሚ ባለሃብት በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ተላልፎ ቢገኝ አግባብ ባለዉ ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

5. ማንኛዉም ባለሃብት የመሬት ከራይ ዉል ዘመን ሲያበቃ ወይም ሲቋረጥ የመሬቱ የተፈጥሮ ኃብት ይዘት እንደተጠበቀ ለሚመለከተዉ አካል በወቅቱ ማስረከብ አለበት።

## 18. ስለተከለሉ ስፍራዎች

1. መንግስት የማዕድን ስፍራዎችንና በአቀማመጣቸውና ሁኔታቸዉ ለብዙሃን ሕይወት ቀጣይነት አስፈላጊ የሆኑ ቦታዎችንና የመሳሰሉትን ከልሎ መያዝ ይችላል። እነዚህ ቦታዎች የሚተዳደሩት አግባብ ባለዉ አካል በሚወጣ ህግ ይሆናል።

2. ጥብቅ መሬቶችን የመከላከል ፣ የመለየት ፣ የማልማት ፣ የማስጠበቅና መልሶ የማቋቋም ተግባር በአካባቢዉ ህብረተሰብ ተሳትፎ እና በመንግስት ይከናወናል።

3. የአካባቢዉ ህብረተሰብ ከተከለሉ እና ከተጠበቁ ሥፍራዎች ከሚገኘዉ ጥቅም ተካፋይ የመሆን መብቱ የተጠበቀ ነዉ።

## 19. በመስኖ ስለሚለሙ መሬቶች

1. ማንኛዉም ዘመናዊ የመስኖ ልማት ከመካሄዱ በፊት የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የሚያወጣቸዉ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነዉ ተፈላጊ የሆኑ ዝርዝር ጥናቶች ፣ ለግድብ ግንባታዎች ተፈላጊዉ የተፋሰስ ልማት ስራ ፣ የማሳ መሰረተ ልማት አዉታርና የግድቡ ደረጃ እና ለግድቡ ስራዎች በሚቆፈሩ የአካባቢ ጥሬ ዕቃዎች /አፈር ፣ ድንጋይ/ ምክንያት በአካባቢዉ ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት የከፋ እንዳይሆን የመከላከያና የጥበቃ ስልቱ ተቀባይነት ማግኘቱ መረጋገጥ አለበት።

2. ማንኛዉም አርሶ አደር ይዞታዉ በመስኖ ግንባታዎች ስር የዋለ እንደ ወንዝ መቀልበሻና የመስኖ ቦይ ያለምንም ካሳ ጥያቄ የመፍቀድ ግዴታ አለበት። ነገር ግን በማሳዉ ላይ ቋሚ ተክሎች ካሉ ካሳ መጠየቅ ይችላል።

3. መንግስትና ተጠቃሚዉ ህብረተሰብ በዘመናዊ መስኖ ልማት ለሚዘረጋዉ የመስረተ ልማት አዉታርና ለተፋሰሱ ተገቢዉን ጥበቃና ልማት የማድረግ ግዴታ አለባቸዉ::

4. ማንኛዉም የመስኖ መሬት ተጠቃሚ በአግባቡና ሳያሳድር ሙሉ በሙሉ መሬትን ጥቅም ላይ የማዋል ግዴታ አለበት::

5. በመስኖ በሚለማ መሬት ላይ የሚተከሉ የዛፍ ዓይነቶች በዉሃ አጠቃቀምና በአጎራባች መሬቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያሳድሩ መሆናቸዉ መረጋገጥ አለበት:: በእንጸሩም ተጠቃሚዎች ለመስኖ ልማት በሚያገለግል ወንዝና በዋና ዋና ቦዮች ዳር በዉሃ አጠቃቀሙና በግንባታ ላይ ጉዳት የማያስከትሉ ቋሚ ተክሎችን ማልማት ይኖርባቸዋል::

6. ማንኛዉም የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ አደር ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ዓመታዊ ሰብል የማልማት ግዴታ አለበት:: አጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት ይህንን የማይተገብር የይዞታ መብቱን ሊያጣ ይችላል::

7. ባህላዊ የመስኖ አጠቃቀምን በተመለከተ የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ምክር እና የአካባቢዉ ህብረተሰብ በዚሁ ላይ ተመስርቶ በሚያወጣዉ ዉስጠ ደንብ /መተዳደሪያ ደንብ/ መሰረት መመራት ይኖርበታል::

## 20. በመሬት ላይ ስለሚነሱ ግጭቶች ፣ አለመግባባቶችና ክርክሮች አወሳሰን

1. ማንኛዉም በእርሻ መሬት ድንበርና ይዞታ ላይ ለሚነሳዉ ግጭት ወይም አለመግባባት ከዚህ እንደሚከተለዉ መፍትሄ እንዲያገኝ ይደረጋል::

   ሀ.በመጀመሪያ ደረጃ የማህበራዊ ጉዳይ ፍ/ቤት በማመልከት ፣

   ለ.የቀበሌዎች የማህበራዊ ሸንጎ ፍ/ቤት በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ካለ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቅሬታን በማሰማት ይሆናል::

2. የወረዳዉ ፍ/ቤት በቀበሌ የማህበራዊ ፍ/ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ አይቶ ካጸደቀ ዉሳኔዉ የመጨረሻ ይሆናል::

3. የቀበሌዉ የማህበራዊ ፍ/ቤትና የወረዳዉ ፍ/ቤት የሚሰጡት ዉሳኔዎች የተለያዩ ከሆነ ቅሬታ ያለዉ ወገን ለከፍተኛዉ ፍ/ቤት ቅሬታዉን ለማሰማት መብት ይኖረዋል:: በዚህ ደረጃ የሚሰጠዉ ዉሳኔዉም የመጨረሻ ይሆናል::

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸዉን እርስ በርሳቸዉ በመስማማት ፣ በሽማግሌዎች ወይም ጥያቄያቸዉን ራሳቸዉ ጉዳዩ ለሚመለከተዉ የመስተዳድር አካል አቅርበዉ መፍትሄ የማግኘት መብት አይገድብም::

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 21. ስለ ቅጣት

ማንኛዉም ሰዉ የፌደራሉን አዋጅ ቁጥር 456 ለማስፈጸም የወጡትን ይህንን ደንብና መመሪያዎችን ተላልፎ ቢገኝ አግባብነት ባለዉ ህግ መሰረት ይቀጣል::

## 22. የመተባበር ግዴታ

ማንኛዉም ሰዉ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም አግባብነት ካላቸዉ አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት::

## 23. ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጎች

በዚህ ደንብ የተጠቀሱትን ጉዳዮች አስመልክቶ ማንኛዉም ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ሁሉ በህግ ተቀባይነት አይኖረዉም

## 24. መመሪያ የማዉጣት ሥልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ለዚህ ደንብ አፈጻጸም መመሪያ የማዉጣት ስልጣን ይኖረዋል::

## 25. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከመጋቢት 2ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**ሐረር መጋቢት 2 ቀን 1998 ዓ.ም**

**ሙራድ አብዱልሃዲ**

**የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ፕሬዝዳንት**